የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 53
ADDIS ABABA 24th July, 2014

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፬/፳፻፮ ዓ.ም

ለድሬዳዋ-ደወሌ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ማስፈፀሚያ ከቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.............................................ገጽ ፯ሺ፬፻፶፮

## CONTENTS

Proclamation No. 854/2014

Export–Import bank of China Loan Agreement for Financing the Diredawa-Dawale Road Project Ratification Proclamation.... .......................Page 7456

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፬/፳፻፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለድሬዳዋ-ደወሌ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፹፯ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ሜይ ፬ ቀን ፳፻፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፱ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 854/2014

## A PROCLAMATION TO RATIFAY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT – IMPORT BANK OF CHINA

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export–Import Bank of China stipulating that the Export–Import Bank of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount equivalent to USD 187,000,000 (One Hundred Eighty Seven Million United States Dollars) for Financing the Diredawa-Dawale Road Project, was signed in Addis Ababa on the 4th day of May 2014;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at session held on the 26th day of June, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለድሬዳዋ - ደወሌ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፬/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ሜይ ፬ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር China Eximbank PBC No. (2014)03 Total No. (297) No.1420303052013211786 የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፹፯ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን 2006 ዓ.ም

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Export – Import Bank of China Loan Agreement for Financing the Diredawa-Dawale Road Project Ratification Proclamation No. 854/2014".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement number China Eximbank PBC No. (2014)03 Total No. (297) No. 1420303052013211786 signed in Addis Ababa on May 4th 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Export – Import Bank of China is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of USD 187,000,000 (One Hundred Eighty Seven Million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 24th day of July, 2014.

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት